ፌብሩወሪ 2018 QuickNotes ቁ. 2

## 2017-2018 የትምህርት ዓመት እስከ ጁን 13 ተራዝሟል

በቅርቡ የተከሰተው ከባድ የአየር ሁኔታ ለሦስት ቀናት (ጃኑወሪ 4፣ ጃኑወሪ 17፣ እና ፌብሩወሪ 7) የ MCPS ት/ቤቶች እንዲዘጉ አስገድዷል። በ 2017-2018 የ MCPS ትምህርት ካላንደር የሚያካትተው 182 የትምህርት ቀናት፣ በሜሪላንድ ስቴት ቢያንስ ከሚጠበቀው ገደብ በሁለት ቀናት የበለጠ ነው። በነዚህ ቀናት ት/ቤቶች በመዘጋታቸው ምክንያት፣ MCPS ከተመደቡት የማካካሻ ቀናት አንዱን ቀን በስቴት-መስፈርት የተመደበውን የትምህርት ቀናት ለማሟላት መጠቀም ይኖርበታል። የትምህርት ዓመቱ አሁን እስከ ጁን 13/2018 ይራዘማል። የመጨረሻው የትምህርት ቀን ለሁሉም ተማሪዎች ቀድመው የሚለቀቁበት ቀን ይሆናል። በአስቸኳይ የአየር ሁኔታ ምክንያት ዳግመኛ ት/ቤት ከተዘጋ ሌሎች ተጨማሪ የማካካሻ-ቀናትን የመጠቀም አስፈላጊነት ያስከትላል። ከዚህ በታች ያለው የቀኖቹን አጠቃቀም ቅደምተከተል ያሳያል፡-

- በአንድ ተጨማሪ የአስቸኳይ አየር ሁኔታ ምክንያት ት/ቤት ከተዘጋ፣ የትምህርት ዓመቱ እስከ ጁን 14/2018 ይራዘማል።
- በሁለት ተጨማሪ የአስቸኳይ አየር ሁኔታ ምክንያት ት/ቤት ከተዘጋ፣የትምህርት ዓመቱ እስከ ጁን 15/2018 ይራዘማል። (ማስታወሻ፡- በስቴት ድንብ መሠረት፣ MCPS የትምህርት ዓመትን ከጁን 15 ማሳለፍ አይችልም)
- በአስቸኳይ የአየር ሁኔታ ምክንያት ሦስት ተጨማሪ ቀናት ት/ቤት ከተዘጋ፣ ማርች 26/2018 ( የስፕሪንግ እረፍት የመጀመሪያውን ቀን/the first day of Spring Break) እንደ ማካካሻ-ቀን እንጠቀማለን።
- በአስቸኳይ የአየር ሁኔታ ምክንያት አራት ተጨማሪ ቀናት ት/ቤት ከተዘጋ፣ ማርች 27/2018 (የስፕሪንግ እረፍት ሁለተኛውን ቀን/the second day of Spring Break) እንደ ማካካሻ-ቀን እንጠቀማለን።

ካውንቲው የበለጠ የአስቸኳይ አየር ሁኔታ ካጋጠመውና ተጨማሪ የትምህርት ቀናትን መዝጋት ካስፈለገ፣ ስቴት የመደበው ቢያንስ 180 የትምህርት ቀናት የሚለው ገደብ እንዲነሣ MCPS ይጠይቃል። ገደብ እንዲነሣ ብቃት እንዲኖር፣ የትምህርት ሥርዓቱ የማካካሻ ቀናትን መጨመር ያለበት በትምህርት ዓመት መጨረሻ ላይ ብቻ ሳይሆን ስለሚደረገው ጥረትና ትጋት ተአማኒነትን ለማሳየት የትምህርት ካላንደሩን በተማሪዎች የትምህርት ቀናት ጭምር የባከኑ ጊዜያትን ማካካስ ይጠበቅባቸዋል።

MCPS መጥፎ የአየር ሁኔታዎችን በአንክሮ እየተከታተለ በትምህርት ቤት ካላንደር ላይ ተጽእኖ የሚያስከትሉ ወቅታዊውን መረጃዎችን ማሳወቅ/ማስተላለፍ ስለ MCPS የት/ቤት ካላንደር/ቀን መቁጠርያ, ድረገጽ፡- http://www.montgomeryschoolsmd.org. ይጎብኙ።

**ለ Montgomery Serves Award ጥቆማ ማቅረቢያ ክፍት ነው**

ለ2018 የMontgomery Serves Awards (ሞንጎመሪ ሽልማቶች ይሰጣል) የእጩዎች ጥቆማ መቀበል ተጀምሯል። እነዚህ ሽልማቶች ወደር የሌለው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላበረከቱ ግለሰቦች፣ ቡድን፣ እና ድርጅቶች እውቅና ይሰጣል። ይህ ስመጥር ዓመታዊ የሽልማት ፕሮግራም፣ የሞንጎመሪ ካውንቲ ለአገልግሎት የሚሰጠው ከፍተኛው የክብር ሽልማት በሚከተሉት ዘርፎች በበጎ ፈቃደኝነት ያገለገሉትን ለማመስገን ነው።

- **የዓመቱ የበጎ ፈቃደኛ ሽልማት፣** በ 2017 ወደር የሌለው የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት በግል ላበረከቱ
- **የዓመቱ የወጣት በጎ ፈቃደኛ ሽልማት፣** እድሜያቸው 18 እና ከዚያ በታች ለሆኑ ወጣት ድንቅ በጎ ፈቃደኞች
- **የዓመቱ በጎ ፈቃደኛ ቡድን ሽልማት** ለቡድኑ ድንቅ የበጎ ፈቃደኝነት ትጋት
- **የዓመቱ የበጎ ፈቃድ ቢዝነስ ሽልማት** የላቀ የማህበረሰብ አገልግሎት ላበረከተ ኮርፖሬሽን
- Neal Potter Path of Achievement Award 60 ዓመት እና ከዚያ በላይ እድሜ ያላቸው ነዋሪዎች በህይወት ዘመናቸው ላበረከቱት ከፍተኛ አገልግሎት

የሽልማቱ ተቀባዮች በኤፕረል ወር በሚካሄደው አመታዊ የMontgomery Serves Awards ሥነ-ሥርዓት እውቅናን ያገኛሉ። የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና የመጠቆሚያ ቅጾችን ለማግኘት ይህንን ድረገጽ ይጎብኙ፡- Montgomery Serves website.

ጥቆማ ለማቅረብ የመጨረሻ ቀን/የጊዜ ገደብ. ዓርብ, ፌብሯሪ 23 5 p.m ነው። ለተጨማሪ መረጃ/ኢንፎርሜሽን፣ ኢ-ሜይል serviceawards@montgomerycountymd.gov ወይም በስልክ ቁጥር 240-777-2600 ይደዉሉ።

ድረገጽ ላይ ጥቆማ ማቅረቢያ ቅጾች

**ቅድሚያ የኮሌጅ አሶሽየት ዲግሪ ፕሮግራም/Early College Associate Degree Program ለመግባት ፍላጎት ለሚኖራቸው የመመዝገቢያ ቅጽ አሁን ተዘጋጅቷል።**

MCPS ከሞንጎመሪ ኮሌጅ (MC) ጋር በመተባበር የመጀመሪያውን ቅድሚያ የኮሌጅ (EC) አሶሽየት ዲግሪ ፕሮግራም/Early College (EC) Associate Degree በ MC ለዲስትሪክቱ በሞላ ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ይሰጣል። EC ፕሮግራም የሚሰጠው በሞንጎመሪ ኮሌጅ ካምፓስ ሮክቪል/MC Rockville campus ሲሆን ለተማሪዎች በአስተማሪነት፣ በሁለተኛ ደረጃ ሂሳብ፣ ወይም አሶሽየት ኦቭ ሳይንስ፣ እንዲሁም በሂሳብ ትምህርት አሶሽየት ዲግሪ የማግኘት አማራጮችን ይሰጣል።

የሚሳተፉት ተማሪዎች ሁለት ዓመት የቅድሚያ ኮሌጅ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ በተመሣሣይ ወቅት የ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ትምህርታቸውንም በአንድ ላይ ለማጠናቀቅ ይችላሉ። ተማሪዎቹ በሚያጠናቅቁበት ወቅት፣ ከ MC አሶሽዬት ዲግሪ እና የሜሪላንድ ስቴት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ያገኛሉ።

በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ተማሪዎች 10ኛ ክፍል ሲጨርሱ ቢያንስ የሚከተለው እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

- ቴክ ክሬዲት እና ፒኢ/ሄልዝ ክሬዲት (Earned Tech credit and PE/Health credit)
- በስቴት ደረጃ የሚሰጠውን የሂሳብ እና የእንግሊዝኛ ምዘና ፈተና መጨረስ፣
- የኮሌጅ ዝግጅት ምዘና የወሰዱ እና ፎል ላይ ካልኩለስ ለመውሰድ የተዘጋጁ፣
- GPA an unweighted 2.75 ወይም የበለጠ ያላቸው፡-
- የተማሪ ሥራ አገልግሎት ትምህርት ተፈላጊ ሠዓቶችን ያጠናቀቁ ወይም ለማጠናቀቅ የተቃረቡ፣
- ዝንባሌ/ፍላጎት እንዳላቸው ቅጽ የሞሉ እና ኢንፎርሜሽን የሚሰጥባቸውን ክፍለጊዜያት የተከታተሉ፣

ፍላጎት/ዝንባሌ ያላቸው ተማሪዎች እና ወላጆች በሙሉ የዝንባሌ/ፍላጎት ማረጋገጫ ቅጽ እስከ ረቡዕ፣ ማርች 7 መሙላት አለባቸው። ተማሪዎች እና ወላጆች ለኢንፎርሜሽን ልውውጥ ክፍለ ጊዜ የግዴታ መሳተፍ አለባቸው ሰኞ፣ ማርች 12 ሠዓት፡- ከ6:30 እስከ 8 p.m በሞንጎመሪ ኮሌጅ ካምፓስ(ግቢ)/MC Rockville campus, 51 Mannakee St., በ Parilla Performing Arts ማዕከል ከ 6:30 እስከ 8 p.m.

የበለጠ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ድረገጽ ይጎብኙ፡- ሁለትዮሽ ፕሮግራም መመዝገቢያ ድረገጽ

**ኮድ መስበር፡- ከለር ልጃገረዶችን በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በምህንድስና እና በሂሳብ ትምህርቶች የበለጠ እንዲሳተፉ የሚያበረታታ/የሚማርክ ሁኔታ መፍጠር/** Girls of Color in STEM(Science, Technology, Engineering and Math)

**የጥቁሮች ታሪክ በሚከበርበት ወር ላይ** MCPS **አንድ ልዩ ዓይነት ዝግጅት ያካሄዳል።**
*ኮድ መስበር፡- ከለር ልጃገረዶችን በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በምህንድስና እና በሂሳብ ትምህርቶች የበለጠ እንዲሳተፉ የሚያበረታታ/የሚማርክ ሁኔታ መፍጠር/Girls of Color in STEM(Science, Technology, Engineering and Math)* **ረቡእ፣ ፌብሩሪ** 28 **ለዚህ አላማ የተዘጋጀ ውይይት**/panel discussion **በጆን ኤፍ ኬኔዲ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኦዲቶሪየም-ሲልቨርስፐሪንግ ላይ ከ** 6 **እስከ** 8 p.m **ይካሄዳል።** (John F. Kennedy High School 1901 Randolph Road, Silver Spring) **ኦዲቶሪየም**

**ውይይቱ የሚያተኩረው፣ ከለር ልጃገረዶች በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በምህንድስና እና በሂሳብ ትምህርቶች እና ፕሮግራሞች የበለጠ እንዲሳተፉ** MCPS **የበለጠ የሚማርክ ሁኔታ ለመፍጠር ለማረጋገጥ እና ለማበረታታት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ነው። በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና፣ እና በሂሳብ/**STEM **ዘርፎች በርካታ እድሎች እያደጉ ከመሄዳቸውም በላይ ለሴቶች አብዛኛውን ጊዜ በሌሎች መስኮች የማይገኙ የኤኮኖሚ እድሎችንም ይሰጣሉ። የሆነ ሆኖ፣ ከለር ሴቶች በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በምህንድስና፣ እና በሂሳብ** (STEM) **መስኮች ያላቸው ተሳትፎ በጣም አነስተኛ ነው። የውይይቱ አቅራቢዎች/ተሳታፊዎች ከለር ልጃገረዶች በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በምህንድስና እና በሂሳብ** STEM **መስኮች በስፋት ለመሳተፍ አንዳንድ እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮችን በመግለጽ በዲስትሪክቱ የቢዝነስ፣ እና የማህበረሰብ ድርጅቶች እነዚህን እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ለማስወገድ የሚችሉበትን መላ ይጠቁማል። በዓሉ/ክውነቱ ነጻ እና ለህዝብ ክፍት ነዉ።**

RSVP

**እንዲሁም…**

**በሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ቤተመጻህፍት/ላይብራሪዎች** (MCPL) **የጥቁር ህዝቦች ታሪክ የሚከበርበት ወር በተከታታይ በሚቀርቡ ልዩ ዝግጅቶች ይከበራል። በነፃ የሚቀርቡ ዝግጅቶች በሚከተሉት ቅርንጫፎች ይካሄዳሉ፡-**

ፌብሯሪ፣ 21 በ 6 p.m
Thurgood Marshall: A Trail-Blazing Civil Rights Victory in Montgomery County
ስለ ሰው ልጆች መብት ተከራካሪ ተምሳሌት የሆነው ተስርጉድ ማርሻል (Thurgood Marshall) በት/ቤት ማግለል/እኩል መብት ማሳጣት እንዲወገድ በቅድሚያ የተቃወመና በ 1937 በዚሁ በሞንጎመሪ ካውንቲ -ለአፍሪካዊያን አሜሪካዊያን መምህራን እኩል ክፍያ እንዲደረግ ታግሏል። በዚህ በስዕላዊ

መግለጫ የተደገፈ ዝግጅት ላይ ስለዚህ አካባቢ ዝርዝር አስደናቂ ታሪክ እና በአገራዊ ደረጃ ያበረከተውን ፋይዳ/አስተዋጽኦ ይብራራል።
Olney, 3500 Olney-Laytonsville Road

ፌብሯሪ 24 በ 2 p.m
**የጥቁሮች ታሪክ የሚከበርበት ወር ከሰዓት በኋላ ፊልም** - Akeelah and the Bee
ይህ የAkeelah Anderson ታሪክ፣ የ11 ዓመት ልጅ ሆና የቃላት ተሰጥኦ ያላት እና በአገራዊ የቃላት ውድድር የተሳተፈች መንፈስን የሚቀሰቅስ አስገራሚ ታሪክ ነው።
Marilyn J. Praisner, 14910 Old Columbia Pike, Burtonsville

ፌብሯሪ 24 በ 2 p.m
**የጥቁሮች ታሪክ የሚከበርበት ወር የቤተሰብ ፊልም** - Remember the Titans **ያስታውሱ።**
የፉትቦል አሠልጣኝ Bill Yoast ቡድኑን እስከ 15 የውድድር ወቅቶች በአሸናፊነት ሲመራ ከቆየ በኋላ ከደረጃው ዝቅ ተደርጎ ሌላ በጣም መንቻካ፣ ሀሳበ ግትር ሰው ተወዳጅ ከነበረው ከ Yoast የተለየ Herman Boone የተባለ ሰው ተተካ። እነዚህ ሁለት ሰዎች ልዩነቶቻቸውን እንዴት አሸንፈው በጠላትነት ቡድን ይተያዩ የነበሩ ወጣቶችን ለሻምፒዮና ማብቃታቸው ተደናቂ የሆነ የአሸናፊነት ታሪክ እንደሆነ ይነገራል። በ T. C. Williams ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት Alexandria, VA በእውነተኛ-የህይወት ታሪክ ላይ የተመሰረተ ፊልም ዝግጅቶች ይካሄዳሉ። ፊልሙን ከተመለከቱት በኋላ ስለ ጥቁሮች እውነተኛ የፍልሰት ታሪክ/virtual reality Google Expedition Kits የበለጠ ለመማር/ለማወቅ ይችላሉ።
Chevy Chase, 8005 Connecticut Avenue

ፌብሯሪ 24 በ 3 p.m
MCPL **የአሰሳ ጉዞ/የሽርሽር ጉዞ/**MCPL Expeditions – Selma to Montgomery **የጀብደኝነት አሰሳ ጉዞ ይጠብቅዎታል።**
ሰናይነት ያለው ጥሩነትን የሚያመለክት የአሰሳ ጉዞ ከ Selma እስከ Montgomery፣ ለሰብአዊ ነፃነት ትግል እንቅስቃሴዎችን የሚመሰክሩ መታሰቢያዎችን ከቦታ ወደ ቦታ እየተዟዟሩ ለማየት ለጉዞ Google Expedition Kit "travel" በመጠቀም በ Selma የተካሄደውን የሰዎች የነፃነት ትግል እና ወደ Montgomery የሚያመራ መንገድ ይጎበኛሉ። ይህንን እውነተኛ ታሪክ ለሚመለከቱ ሰዎች አዳዲስ ቦታዎችን እንዲያስሱ እና በሰብአዊ የነፃነት ትግል ዘመቻ ስለተሳተፉት ወንዶች እና ሴቶች እና የሰላማዊ ትግል ጉዞ ለምን አስፈላጊ እንደነበረ ለመማር እድል ይኖራቸዋል። ከጀብደኝነት አሰሳ ቀጥሎ Selma የሚታዩ ነገሮች ይኖራሉ።
Maggie Nightingale, 19633 Fisher Avenue, Poolesville

ፌብሯሪ 26፣ በ 5 p.m
**የጥቁሮች ታሪክ የሚከበርበት ወር ፊልም ምርጫ**-Hidden Figures
የተደበቁ እውቅ ሰዎች ስለ Katherine G. Johnson፣ Dorothy Vaughan፣ እና Mary Jackson፣ ሦስቱ አንፀባራቂ/ድንቅ አፍሪካዊ - አሜሪካዊ ሴቶች NASA ውስጥ እየሰሩ ከከፍተኛ ታሪካዊ ክንውኖች አንዱ የሆነውን ጠፈረተኛ John Glenn ወደ ምህዋር እንዲመጥቅ ሲደረግ ከድርጊቱ በስተጀርባ ጭንቅላት/አእምሮ በመሆን ማገልገላቸውን ይመሰክራል።
Silver Spring, 900 Wayne Avenue

የበለጠ መረጃ ለማግኘት Mary Ellen Icaza በስልክ ቁጥር 240-777-0006 ያነጋግሩ።

**ስድስተኛው ዓመታዊ የ Ivymount Special Needs Resource Fair ማርች 11 ይካሄዳል።**

በ አይቪማውንት ት/ቤት (Ivymount School) 6ኛው ዓመታዊ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የመገልገያ-መጠቀሚያ ዝግጅት የሚቀርብበት ቀን (Special Needs Resource Fair) እሁድ ማርች 11 ከእኩለ ቀን እስከ 3 p.m ይካሄዳል። በዲ.ሲ ሜትሮፖሊታን አካባቢ ልዩ እርዳታ/ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ልጆች እና ጎልማሳ ወጣቶች ልዩ ልዩ ዓይነት ድጋፍ የሚያደርጉ ከ50 በላይ ኤግዚቢሽኖች ለህዝብ ዕይታ ይቀርባሉ። ዝግጅቱ ለህዝብ ነጻና ክፍት ነው። የ Ivymount አድራሻ፦ 11614 Seven Locks Road in Rockville